# የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድyኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

# የምግብ ማስተዋወቅ ቁጥጥር መመሪያ

ነሐሴ 2004 ዓም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

ማስታወቂያ ሕብረተሰቡ በምርት ግብይት ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች በመወሰን ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤

በማስታወቂያ ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ለህብረተሰቡ የሚያሰራጩት የምግብ ማስታወቂያ ስነ ምግባርን በተከተለ መንገድ እንዲመራ በማስፈለጉ፤

ማንኛውም ለህብረተሰቡ የሚቀርብ የምግብ ማስታወቂያ በቅድሚያ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠና ዘርፉ የሚመራበትን መሰፈርት ያJላ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣኑ አዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀፅ 55 (3) መሰረት ይህ የምግብ ማስተዋወቅ ቁጥጥር መመሪያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የምግብ ማስተዋወቅ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 5/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡

1. "ምግብ" ማለት ማንኛውም በጥሬነቱ፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀ ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ቀርቦ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን ወይም ሌላ መጠጥ፣ የሚታኘክ ማስቲካ፣ ተጨማሪ ምግብ እንዲሁም ምግብ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማከምና ማንኛውም ንጥረ ነገር የሚያካትት ሆኖ ትንባሆና ለመድኃኒትነት ብቻ የሚያገለግሉ ንጥረ ነገሮችን አይጨምርም ፡
2. "የጨቅላ ሕጻን ምግብ" ማለት ከእንስሳ ወይም አትክልት የሚገኝ ወተት ወይም ወተት መሰል ውጤት ሆኖ በኮዴክስ አልመንተሪየስ የጨቅላ ሕጻን ምግብ ደረጃ መሰረት በፋብሪካ የተዘጋጀና ከውልደት እስከ መጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ላለ የጨቅላ ሕጻን የንጥረ ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት የተዘጋጀ ምግብ ነው፡
3. "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት በምግብ ንግድ ሥራ ላይ የሚሰማራ ድርጅት አስፈላጊውን ድርጅታዊ መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነዉ ፡
4. "ተጨማሪ ምግብ" ማለት ማንኛውም መደበኛ አመጋገብን የንጥረ ምግብ ፍላጎት ለማሟላት የሚዘጋጅ የንጥረ ምግብ ወይም ፊዚዮሎጂካል ውጤት ያላቸው የቫይታሚን ወይም የማዕድን ወይም የሌሎች ንጥረ ነገሮች በነጠላ ወይም በጣምራ የሚገኙበትና በተወሰነ መጠን እንዲወሰድ ታስቦ በካፕሱል፣ በእንክብል፣ በዱቄት፣ በፈሳሽ፣ በጠብታ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ የሚዘጋጅ ምግብ ነው ፡

5. “የምግብ ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት” ማለት እንደቅደም ተከተሉ ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ወይም ለአገር ውስጥ ለሚመረት ምግብ ይዘቱን የሚገልጽና ደህንነቱን የሚያረጋግጥ አግባብ ባለው የውጪ አገር አካል ወይም በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ሰነድ ነው ፡

6. "ጤናማ የአመጋገብ ስርዓት" ማለት አንድ ሰው በቀን መውሰድ ያለበት የምግብ ዓይነት ወይም የምግብ ንጥረ ነገር በትክክለኛና ተቀባይነት ባለው መልኩ የአመጋገብ ስርዓት ወይም አሰራር ተከትሎ የሚወሰድ የአመጋገብ ሂደት ነው ፡

7. “የምግብ ማስታወቂያ” ማለት ምግብ፣ የምግብ አገልግሎት፣ የምግብ ድርጅት ስም፣ አርማ፣ ምልክት፣ አላማ ወይም ሌላ ተዛማጅ መልዕክት እንዲተዋወቅ ወይም እንዲሸጥ በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ የሚሰራጭ መልዕክት ነው ፡

8. “የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ” ማለት ማስታወቂያ ለማሰራጨት የሚያገለግል ሲሆን መገናኛ ብዙሃንን፣ የውጭ ማስታወቂያን፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የፖስታ፣ የኢንተርኔት ድረ ገፅ እና የፋክስ አገልግሎትን፣ ሲኒማን፣ ፊልምን፣ ቪዲዮ፣ ኔትዎርኪንግ እና መሰል የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን ይጨምራል ፡

9. “የማስታወቂያ ወኪል” ማለት ከሚመለከተው አካል የማስታወቂያ ሥራ የንግድ ሥራ ፈቃድ በማውጣት በማስታወቂያ ሥራ የተሰማራ ሰው ነው ፡

10. “የማስታወቂያ አሰራጭ” ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የአየር ጊዜ፣ የሕትመት ሽፋን ወይም መሰል አገልግሎት በመስጠት ማስታወቂያ የሚያሰራጭ ሰው ነው ፡

11. “የማስታወቂያ አስነጋሪ” ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት ምርቱ፣ አገልግሎቱ፣ ስሙ፣ አርማው፣ ምልክቱ፣ አላማው ወይም ሌላ መልዕክት የሚነገርለት ወይም የሚተዋወቅለት ሰው ነው ፡

12. “ፕሮግራም” ማለት በድምፅ ወይም በምስል ወይም በሁለቱም ተቀነባብሮ ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ በብሮድካስት አገልግሎት የሚቀርብ የፕሮግራም ስርጭት ነው ፡

13.“መገናኛ ብዙሃን” ማለት በየጊዜው የሚወጣ ሕትመትንና የብሮድካስት አገልግሎትን የሚያካትት ነው ፡

14.“የውጭ ማስታወቂያ” ማለት በውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳ፣ በቢልቦርድ፣ በኤሌክትሮኒክ ስክሪን ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል፣ በተተከለ ነገር፣ በግድግዳ፣ በሕንጻ ወይም በትራንስፖርት ላይ በሚፃፍ፣ በሚተከል ወይም በሚለጠፍ ማስታወቂያ፣ በተንጠልጣይ ነገር፣ በፖስተር፣ በጨርቅ፣ በፕላስቲክ፣ በተባዛ በራሪ ወረቀት ላይ የሚፃፍ ማስታወቂያ፣ በእቃ መያዥ ወይም ማሸጊያ፣ በድምጽ ካሴት፣ በድምፅ ማጉያ መሳሪያ እና በሌላ መሰል የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ ማስታወቂያ ነው ፡

15.“በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራም” ማለት ፕሮግራሙን ለማሰራጨት ገንዘብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተከፈለበት ወይም የክፍያ ቃል የተገባበት ፕሮግራም ነው ፡

16.“ስፖንሰር” ማለት በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራምን ስፖንሰር የሚያደርግ ሰው ነው ፡

17.“ፕሮግራም” ማለት በድምፅ ወይም በምስል ወይም በሁለቱ ተቀነባብሮ ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ በብሮድካስት አገልግሎት የሚቀርብ የፕሮግራም ስርጭት ነው ፡

18.“የምግብ ንግድ ድርጅት” ማለት በምግብ ማምረት፣ መላክ፣ ማስመጣት፣ ጅምላ ማከፋፈል ወይም ችርቻሮ ንግድ ስራ የተሰማራ ድርጅት ነው ፡

19.“አግባብ ያለው ተቆጣጣሪ አካል” ማለት ይህ ስያሜ የተጠቀሰበት ድንጋጌ በሚነካው ጉዳይ ላይ በሕግ የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው የፌዴራል ወይም የክልል የመንግስት አካል ነው ፡

20."አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድሀኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661/2002 ነው ፡

21.“ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሀኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው ፡

22.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በሀገራችን በተለያየ የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገዶች የሚሰራጩ የምግብ ማስታወቂያዎችን እውነተኛነትና ተአማኒነት በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገራችን የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገዶች የሚሰራጩ የምግብ ማስታወቂያዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ምግብን ስለ ማስተዋወቅ

## 5. ስለ ምግብ ማስታወቂያ አስነጋሪ

ማንኛውም የምግብ ማስታወቂያ ለማሰራጨት የማስታወቂያ አስነጋሪው ድርጅት ለሚያስተዋውቀው ምግብ በባለስልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል ተቆጣጣሪ አካል ምግብን ለማምረት፣ ለማስመጣት፣ ለማከፋፈል፣ ለመቸርቸር ወይም አገልግሎት ለመስጠት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

## 6. ስለ ምግብ ገላጭ ፅሁፍ

1. ማንኛውም የሚተዋወቅ ምግብ ገላጭ ፅሁፍ ስለ ምግቡ ትክክለኛ ይዘትና ባህሪ የሚገልፅ ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ መሆን አለበት !

   ሀ/ የምግቡ መጠሪያ ስም !

   ለ/ በምግቡ ውስጥ ያለው የንጥረነገሮች ዝርዝር ይዘትና መጠን !

ሐ/ የምግቡ የተጣራ ክብደት !

መ/ የምርት መለያ ቁጥር (batch number) !

ረ/ ምግቡ የተመረተበትንና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ጊዜ! እና

ሰ/ የአምራች ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፡፡

2. በማንኛውም የምግብ ማሸጊያ ገላጭ ፅሁፍ ላይ ስለ ምግቡ ይዘት ወይም የሚሰጠው ጥቅም አጋንኖ ሊያሳይ የሚችል ፅሁፍ ወይም ምስል መኖር የለበትም፡፡

3. ምግቡ የተጨረረ፣ ልውጥ ህያው ወይም ተጨማሪ ምግብ ከሆነ ይኸው በገላጭ ፅሁፉ ላይ መገለፅ አለበት፡፡

## 7. ስለ ምግብ ማስታወቂያ መረጃ

ማንኛውም የምግብ ማስታወቂያ፦

1. በምግቡን ወይም በምግቡ ውስጥ ያለውን ይዘት ለማስተዋወቅ በአምራቹ የተሰጠውን ትክክለኛ መጠሪያ ስም መሆን አለበት፡፡

2. የምግቡን ይዘት፣ ምስል፣ ጥቅም፣ ባህሪ፣ መአዛ፣ ጣእም፣ ንጥረ ነገርና ሌሎች መረጃዎች እውነተኛ፣ በመረጃ የተደገፉና ተጠቃሚውን ሊያሳስቱ የማይችሉ መሆን አለባቸው፡፡

3. ምግቡ የሌለውንና የማይሰጠውን ጥንካሬ፣ እድሜ ወይም ብርካቴ እንዳለው አስመሰሎ ማቅረብ የለበትም፡፡

4. የሰውን ጤና ሊጎዳ ከሚችል እና የባለስልጣኑን ሕግና መመሪያዎች ከሚጻረር፣ አሳሳች ከሆነ ወይም ተገቢ ካልሆነ ይዘት ወይም አቀራረብ ነጻ መሆን አለበት፡፡

5. በማስታወቂያው ውስጥ ትክክለኛና ጤናማ የአመጋገብ ስርዓትን የሚቃረን፣ ከመጠን በላይ ወይም በታች መመገብን የሚገፋፋ ምስል፣ ድምፅ ወይም ፅሁፍ መያዝ የለበትም፡፡

6. በማንኛውም ሁኔታም ቢሆን ምግቡ ከሌላው ወይም ተመሳሳይ ሌላ ምግብ የተሻለ እንደሆነ ተደርጎ መግለፅ አይቻልም፡፡

7. በትክክለኛ ሰነድና ማረጋገጫ ማስረጃ ያልተደገፈ ወይም ያልተረጋገጠ እንደ "ብቸኛ"፣ "ለመጀመሪያ ጊዜ"፣ "ከዚህ ቀደም ያልነበረ"፣ "የሁሉም ምርጫ"፣ "ለሁሉም ተስማሚ"፣ "ልዩ"፣ "አንደኛ"፣ "ተቀባይነት ያገኘ" ወይም ሌላ መሰል የተጋነነ አበላላጭ ይዘት ያለውን ቃል ወይም ምስልን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

8. ምግቡ በተለየ መልኩ ለጤና ወሳኝ እንደሆነ ተደርጎ የሰውን አመለካከት ሊስብ በሚያስችል መልኩ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

9. ሌሎች የምግብ ዓይነቶችን እንደሚተካ ወይም ሌሎች ምግቦች መመገብን አሳንሶ የሚያሳይ መሆን የለበትም፡፡

10. ከፍተኛ የስኳር፣ የጨው ወይም የቅባት መጠን ያለውን ምግብ አነስተኛ መጠን እንዳለው፣ ነፃ ወይም ለጤና ተስማሚ እንደሆነ በማስመሰል ወይም በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያበረታታ መሆን የለበትም፡፡

11. ምግቡ በሽታን እንደሚያድን ወይም እንደሚፈውስ ተደርጎ መገለፅ የለበትም፡፡

12. ህብረተሰቡ በቀላሉ ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ፣ አቀራረብና ይዘት መሆን አለበት፡፡

## 8. አጋዥ መረጃዎች፣ ሽልማቶችና ሌሎች ሰነዶች ስለ መጠቀም

1. ከባለስልጣኑ እውቅናና ፈቃድ ውጪ ወይም ይህንን ተግባር ለማከናወን በህግ ስልጣን ከተሰጠው ሶስተኛ ወገን ውጪ ስለ ምግቡ ይዘት፣ ጥራትና ደህንነት ወይም ሌላ የምርመራ ውጤቶች የሚቀርቡ ገላጭ መረጃዎችን እንደ አጋዥ ማስረጃ ተደርገው መውሰድ የተከለከለ ነው፡፡

2. የግለሰብ አስተያየት፣ ምስክርነት ወይም መረጃ በመጠቀም ስለ ማንኛውም የምግብ ጣእም፣ ይዘት ወይም ጥቅም ማስተዋወቅ አይቻልም፡፡

3. ድርጅቱ ከምግቡ ጋር በተያያዘ የተሸለማቸውን ማንኛውም ዓይነት ሽልማቶች በማስታወቂያው ላይ የሚገለፅ ከሆነ ሽልማቱን የሰጠው አካልና የተሰጠበት ምክንያት መገለፅ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (3) ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ሽልማቱ የተሰጠበት ምክንያትና መስፈርት እስካሁን የተጠበቀ ስለ መሆኑ ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል፡፡

5. ስለ ምግቡ ተጠቃሚዎች ብዛት የሚገለፅ ከሆነ መረጃው በትክክለኛ ጥናት የተደገፈና የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

6. የምርምርና የሙከራ ውጤትን ከሳይንሳዊ፣ ቴክኒካዊ ወይም ከሌላ ሕትመት የተወሰደ ጥቅስን ወይም ቃልን ከሚተዋወቀው ምግብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሳይኖረው እንዳለው አስመስሎ ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው፡፡

7. በባለስልጣኑ መስሪያቤት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣ ሰርተፊኬት ወይም ሌላ መረጃ በማንኛውም መንገድ ቢሆን ለፕሮሞሽን ወይም ለማስተዋወቅ አገልግሎት መጠቀም አይችልም፡፡

## 9. ማበራታቻ ነገሮችን ለማስተዋወቂያነት መጠቀም

1. ማንኛውም ከፍተኛ የስኳር፣ ጨው፣ ቅባት ወይም ሌላ የሰውን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ንጥረ ነገር የያዙ ምግቦች ለማስተዋወቅ እንደ ሽልማት፣ ስጦታ ወይም በሌላ መልኩ ምግቡ እንዲሸጥ የሚገፋፉ ማበራታቻ ነገሮች መጠቀም አይቻልም፡፡

2. ማንኛውም ሰው ተጨማሪ ምግብ፣ ልውጥ ህያውና የተጨረረ ምግብ በኔትዎርኪንግ ወይም ተመሳሳይ የግብይት ስርዓት ተጠቅሞ እንዲሸጥለት መገፋፋት ወይም በተለየ መልኩ የማሳመን ስራ መስራት የተከለከለ ነው፡፡

## 10. ስለ አልኮል መጠጥ ማስታወቂያ

1. ማንኛውም የአልኮል ማስታወቂያ የአልኮል መጠጥን መውሰድ ወይም መጠቀም ለጤና ተስማሚ እንደሆነ፣ ግላዊ ወይም ማኅበራዊ ስኬትን እንደሚያስገኝ፣ ጓደኝነት እንደሚፈጥር፣ ለተሻለ ሥነ ልቦናዊ ወይም ለአካላዊ ብቃት እንደሚጠቅም፣ የፈዋሽነት ባህሪ እንዳለው፣ ለግብረስጋ ግንኙነት የተለየ ብቃት እንዳለው፣ የንጥረ ነገሮቹን በጎነት የሚገልጽ፣ በተደጋጋሚ ወይም ከመጠን በላይ መወሰድን የሚገፋፋ ወይም ይህን መሰል መልእክት የሚያስተላልፍ መሆን የለበትም፡፡

2. የአልኮል ማስታወቂያ ከአልኮል ሱስ መቆጠብን የሚያጣጥል ወይም የሚቃወም መሆን የለበትም፡፡

3. ማንኛውም የአልኮል ማስታወቂያ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን የማስታወቂያ አቅራቢ ወይም ተዋናይ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

4. በማንኛውም የአልኮል ማስታወቂያ የአልኮል መጠጡ ለአካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ የማይሸጥ ወይም የተከለከለ እንደሆነ መግለፅ አለበት፡፡

5. የአልኮል መጠኑ ከ12 በመቶ በላይ የሆነ ማንኛውም መጠጥን የሚመለከት ማስታወቂያ ከውጭ ማስታወቂያ በስተቀር በሌሎች የማስታወቂያ ማሰራጫ ወይም ማስተላለፊያ መንገዶች አማካኝነት ማሰራጨት ወይም ማስተላለፍ አይቻልም፡፡

6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) ስር የተደነገገው ቢኖርም ማስታወቂያው በኤሌክትሮኒክ ስክሪን፣ በድምፅ፣ በድምፅ ማጉያ፣ በድምፅ ካሴት ወይም በሌላ በምስልና በድምፅ በሚሰራጭ ወይም በሚተላለፍ የውጭ ማስታወቂያ ሊሰራጭ ወይም ሊተላለፍ አይችልም፡፡

7. በአልኮል መጠጥ ላይ የሚለጠፍ ወይም የሚፃፍ መልእክት፣ ስእል፣ የምርት መለያ ምልክት፣ የካርቱን ስእል፣ ማሸጊያ፣ ወይም ሌላ የአቀራረብ መንገድ በተለየ ዲዛይን ለልጆች እንደተሰራ ወይም ከለስላሳ መጠጥ ጋር በሚመሳሰል መልኩ መቅረብ የለበትም፡፡

8. የአልኮል መጠጥ በማንኛውም ለሰው ልጅ አደገኛ በሆነ ወይም ደህንነቱ ያልተጠበቀ ስራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ባለበት ሁኔታ ይህንን ለመወጣት አጋዥ እንደሆነ ተደርጎ መተዋወቅ የለበትም፡፡
9. የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ በብሮድ ካስት ላይ በሚሰራጭ የልጆች ፕሮግራም ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው፡፡

## 11. ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ስለሚመለከት የምግብ ማስታወቂያ

ማንኛውም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን መሰረት አድርጎ የሚሰራጭ ወይም የሚተላለፍ ማስታወቂያ፣

1. የልጆችን እድሜ፣ እውቀት፣ የብስለት ደረጃን ማእከል ያደረገና ሊረዱት በሚችል ቋንቋና የአቀራረብ ዘይቤ መቅረብ አለበት፡፡

2. የልጆችን አመለካከት፣ ስሜትና አስተሳሰብ ሊጎዳ የሚችልና ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዲያዘነብል የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

3. በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ዋጋን በመግለጽ ምግቡ በማናቸውም ቤተሰብ ሊገዛ እንደሚችል ወይም ለልጆች የተለየ የዋጋ ቅናሽ እንደተደረገ የሚያስመስል እምነት በልጆቹ አእምሮ ሊያሳድር የሚችል መሆን የለበትም፡፡

4. የተዋወቀውን ምግብ የተጠቀመ ልጅ ምግቡን ካልተጠቀመ ልጅ በላይ የአካላዊ፣ የማህበራዊ ወይም አእምራዊ ጠቀሜታ ወይም ብልጫ እንዳለው የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

5. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) እንደተጠበቀ ሆኖ ምግቡ በልጁ ጤና ላይ የሚኖረውን ጠቀሜታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ባለስልጣኑ ምግቡን እንዲተዋወቅ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

6. በቀጥታ ለአካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ተብሎ ባልተዘጋጀ ምግብ ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ድምጽ፣ ምስል ወይም ጽሁፍ የሚያሳይና ሌላ መሰል ይዘት ወይም አቀራረብ የያዘ መሆን የለበትም።

7. ወላጆች በልጆቻቸው ጤናማ የአመጋገብ ስርዓት የሚኖራቸውን የምክርና አሰተምህሮ ሚናን አሳንሶ የሚያሳይ መሆን የለበትም፡፡

8. ልጆች የቅንጦትና ፈጣን ምግብን (fast food) ከመጠን በላይ እንዲወስዱ ወይም በመደበኛና ጤናማ የአመጋገብ ስርዓት ምትክ እንዲመገቡ የሚያበረታታ መሆን የለበትም፡፡

## 12. ስለ ጨቅላ ህፃን ምግብ

1. ማንኛም የጨቅላ ህፃን ምግብ በምግቡ ማሸጊያ ገላጭ ፅሁፍ ከመለጠፍ በስተቀር በማንኛውም የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገዶች ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው፡፡
2. ማንኛውም ሰው ለእርጉዝ ሴቶች፣ የጨቅላ ህፃናት እናቶች ወይም የቤተሰብ አባል የጨቅላ ህፃን ምግብ ናሙና ወይም ስለ ምግቡ የሚገልፁ ማንኛውም ዓይነት ስጦታ፣ እቃ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገር መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

3. በማንኛውም የጨቅላ ህፃናት ምግብ ስለ ምግቡ ጠቀሜታና አስፈላጊነት ሊያሳይ ወይም ሊገልፅ የሚችል የተጋነነ ስእል ወይም ሌላ ፅሁፍ በማስታወቂያው ላይ መኖር የለበትም፡፡

5 በምግቡ ገላጭ ፅሁፍ ላይ ከእናት ጡት ወተት የበለጠ፣ የማይተናነስ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አበላላጭ ቃል ወይም ሀረግ በመጠቀም ተመራጭ እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ የተከለከለ ነው፣

6 ማንኛውም የጨቅላ ህፃናት ምግብ የሚሸጥበት፣ የሚሰራጭበት ቦታ ወይም ሱቅ ምግቡን በቀጥታ ሰው እንዲገዛው ሊያነሳሱ የሚያስችሉ የማስታወቂያ መንገዶች እንደ ናሙና መስጠት፣ የተለየ የማስታወቂያ ወይም ማሳያ መንገድ መጠቀም፣ "የዋጋ ቅናሽ" ፣ "ልዩ" ወይም "የማጣሪያ ሽያጭ" የሚሉ መልእክቶች መለጠፍ ወይም ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

## 13. በስፖንሰር ስለሚቀርቡ የምግብ ማስታወቂያዎች

1. በስፖንሰር አማካኝነት የሚቀርብ የምግብ ማስታወቂያ ይዘት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ያከበረ መሆን አለበት፡፡
2. በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ስፖንሰር የተደረገው ፕሮግራም አቅራቢ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ ከፀደቀ ማስታወቂያ ውጪ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ፍላጎት የስፖንሰሩ ምግብ እንዲሸጥ ማነሳሳት የለበትም፡፡
3. የአልኮል መጠኑ ከ12 በመቶ በላይ የሆነ መጠጥ የሚያመርት ወይም የሚሸጥ ሰው ስፖንሰር ሊሆን አይችልም፡፡

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 14. መረጃን ስለማረጋገጥ

ማንኛውም የማስታወቂያ አሰራጭ አካል በማስታወቂያ አስነጋሪው ወይም ወኪል የቀረበለትን መረጃ ትክክለኛነትና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች የተከበሩ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

## 15. የመተግበር ግዴታ

1. ማንኛውም ማስታወቂያ አሰራጭ ሰው የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የመተግበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ አስተላላፊ ወይም አሰራጭ አካላት በለስልጣኑ ሲጠይቅ አስፈላጊውን መረጃና የተላለፈው ማስታወቂያ ኮፒ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

## 16. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ ሰርኩላር ደብዳቤ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከተ ጉዳይን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 17. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አቶ የሁሉ ደነቀው**

**የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**